## ከዘመዶቻቸው ጓደኞቻቸውና ወዳጆቻቸው

የብስንም ተጉዘህ ባሕር አቋርጠህ
ከትብት መቀበሪያ ከእናት አገርህ
ተሰደህ የሄድከው እደዚያ እርቀህ
ከኬንያ ኖርወይ ብሎም አሜሪካን የተሸጋገርህ
ለሞት አልነበረም መንግስቱ አላማህ።

ብቁ ባለሞያ የሕግ ኤክስፐርቱ
ለፍትህ ዲሞክራሲ በጥናት መሟገቱ
በጥልቅ የአገር ፍቅር የአላማ ጽናቱ
እራሱን አርቆ ከሹመት ከሐብቱ
ሲታገል ነበረ እስከ ለተ ሞቱ
ሞት በስደት ሆነ ከአገሩ መውጣቱ ።

በእናት አገርህና በኖርዌይ አሜሪካ
የተማርከው ትምህርት እውቀትህ ሲለካ
ከኢትዮጵያም አልፎ ለአለም ለአፍሪካ
የሚጠቅም ነበር እጅግ የሚያረካ
ከሞት አያመልጥም የሕግ ሰውም ለካ።

ለኔ ብሎ መኖር ያልፈጠረብህ
አገሬ ወገኔ ሁልጊዜም እንዳልክ
በትግል ተወልደህ በትግል ኖረህ
ከመስመር ሳትወጣ ጥቅም አሸንፎህ
እንደቃልህ ሆነ መንግስቱ ሞትህ

መንግስቱ ዋሲሁን ነበረ ስምህ
በሞት ሳትረታ በዓለም ስምህ።

ፍትሕ ዲሞክራሲ በአገር እንዲሰፍን
መንግስቱ ከትግል ሳያጥፍ ግንባሩን
በስደት ሞት ሞተ የማይቀረውን